INTERMEM

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ማ/ቅ/ጽ/ቤት
EHTIOPIAN REVENUE AND CUSTOMS AUTHORITY
A.A. KAIITY CUSTOMS BRANCH OFFICE

የውስጥመጻጻፊያ
መጻጻፊ.ያ

ቁጥር፡ ም/ሥ/የአድ/0035/09

ቀን፡ 17/04/2009 ዓ.ም

ለ፡- ጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም የሥራ ሂደት

ለ፡- ሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት

ለ፡- ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የሥራ ሂደት

ለ፡- ጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት

ለ፡- ደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት

ከ፡- ጉምሩክ ጉዳዮች ም/ስራ አስኪያጅ

አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

የጉምሩክ ጉዳዮች ም/ስራ አስኪያጅ

በቁጥር 3.1.0/357/09 ቀን 13/04/2009 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የብረታ ብረት ማነፃፀሪያ ዋጋዎች አፈፃፀም ማሻሻያ አሰራር በተሰጠው የአሰራር ማብራሪያ መሰረት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ እና ዲ/ዮናቸው በዋጋ ምክንያት በእንጥልጥል ላይ የሚገኙ ብረታ ብረቶች የክፍያ ስርዓቶች በማየት በተገዛበት ቀን ወይም ዴቤት ኖት እየታየ ይሰራበት የነበረው አሰራር የቀረ መሆኑ ቀርቶ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 እና በመመሪያ ቁጥር 111/08 በተደነገገው የዋጋ አተማመን ዘዴዎች በቅደም ተከተል እንዲፈፀም በተገለፀልን መሰረት በዚሁ አግባብ እንዲፈፀም እያሳሰብኩ የዋጋ መረጃ ማነፃፀሪያ አጠቃቀም በተመለከተ ከዳይሬክቶሬቱ በተላከው ሰርኩላር መሰረት እንዲፈፀም በኢሲቪኤስ ውስጥ የሚገባው መረጃ ጥራትና ወጥነት ለማስጠበቅ ሁሉም ዲ/ዮን አቅራቢዎች ወደ ቪዲዲ እና አሲኩዳ ውስጥ የሚያስገቡትን ዕቃዎች ክብደት መለኪያና ብዛት መጠን በኩሎግራም ብቻ መሆኑን በማረጋገጥ እንድትሰሩ እያሳሰብኩ የተላከውን 1 ገጽ ደብዳቤ በአባሪነት አያይዘን ልከንላችኋል፡፡

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፣

- ለሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
- ለሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ስራዎች ም/ሥራ አስኪያጅ

አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

855
ጉ.ሻ.ል
1628 ሰ/ረ
01
ፋይት

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር 3-1-0 1357/09
Ref. No
ቀን 13 ታህሣ 2009
Date

ለጉምሩክ ሥነሥርዓት የሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

በያሉበት፤

ጉዳዩ፡ የብረታብረት ማነፃፀሪያ ዋጋዎች አፈፃፀም ማሻሻያ አሠራር መላክን ይመለከታል፡፡

ከዚህ በፊት የብረታ ብረት ማነፃፀሪያ ዋጋዎች አፈፃፀም አስመልክቶ በቁጥር 4.1.2/30/4/01 በቀን 11/7/2001 ዓ.ም. እና በቁጥር 4.1.2/59/8/02 በቀን 14/04/2002 ዓ.ም. በተፃፉ ደብዳቤዎች በL/C፣ CAD፣ T/T የክፍያ ሥርዓቶች ተገዝተው ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ እንዴት መስተናገድ እንዴት እንደሚገባቸው በተላለፈው አሠራር መሠረት እየተሠራ መቆየቱ ይታወቃል፡፡

ይሁን እንጂ በቁጥር የጉ/ገ/አ/አ/313/09 በቀን 18/02.09 ከጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ፅ/ቤት በተፃፈ የውስጥ ለውስጥ ማስታወሻ በቁጥር 4.1.2/59/8/02 በቀን 14/04/2002 ከዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ ዳይሬክቶሬት በኩል በCAD (Cash against Document) ለሚገዙ ብረታብረቶች የዋጋ አሰራርን አስመልክቶ ለቅ/ጽ/ቤቶች ለተላከ ሠርኩላር እስካሁን በስራ ላይ ስለመሆኑ እና ከአዋጅ ቁጥር 859/2006 ካለው የዋጋ አተማመን ድንጋጌዎች አንፃር ያለውን ተገቢነትና እንዴት እንደሚጣጣም ማብራሪያ እንድንሰጥበት በጠየቀው መሠረት ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም አንድአንድ የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች እና ተገልጋዮች ተመሳሳይ ጥያቄዎች በመቅረብ ላይ በመሆናቸው በሥራ ላይ ካለው ህግ አንፃር ታይቶ ይህ የማሻሻያ አሠራር መላክ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከጥያቄው አንፃር በአዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀፅ 181 ንኡስ አንቀፅ 3 ላይ "...ነባር ደንቦችና መመሪያዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ አዲስ ደንቦችና መመሪያዎች እስኪተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል" ይላል፡፡ በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀፅ 180 ንኡስ አንቀፅ 2 ላይ በተሰጠው ስልጣን መሰረት አዲስ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 111/08 አውጥቷል፡፡

በአዋጁ እና በመመሪያው መሠረት የጉምሩክ ዋጋ ለመወሰን በስድስቱ የዋጋ አተማመን ዘዴዎች በቅደም ተከተል በመጠቀም በሥጋት ሥራ አመራር መርህ መሠረት ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ሊሆን እንደሚገባው ይደነግጋል፡፡ በዚሁ የህግ አግባብ መሠረት የገባውን ዕቃ በግብይት ዋጋ አተማመን ዘዴ በመጠቀም መወሰን ባልተቻለበት ወቅት ዕቃው ከመግባቱ በፊት በ90 ቀናት ውስጥ በተመሳሳይ የንግድ ደረጃ እና በተቀራራቢ ብዛት ወደ አገር ውስጥ ገብተው በጉምሩክ በኩል ተቀባይነት ያገኙ የአንድ ዓይነት እና የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ በማነፃፀሪያነት በመጠቀም ትክክለኛነቱን በማጣራት ሊወሰን እንደሚገባው ይገልፃል፡፡



ስልክ ቁ / Tel.. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

በተጨማሪም በመመሪያ ቁጥር 111/2008 ዓ.ም. በአንቀፅ 44 ላይ "የገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 94/2006 እና ከዋጋ አተማመን ጋር በተያያዘ ይሰራባቸው የነበሩ ልምዶችና አሰራሮች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል" ይላል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ከዚህ በፊት የብረታ ብረት ማነፃፀሪያ ዋጋዎች አፈፃፀም አስመልክቶ በቁጥር 4.1.2/30/4/01 በቀን 11/7/2001 ዓ.ም. እና በቁጥር 4.1.2/59/8/02 በቀን 14/04/2002 ዓ.ም. በተፃፉ ደብዳቤዎች መሠረት የL/C የተከፈተበት ቀን እየታየ፣ በCAD፣ T/T የክፍያ ሥርዓቶች ተገዝተው ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ ደቢት ኖት ቀን (Debit Note date) እየታየ በዚሁ ወቅት ካለው የዓለም አቀፍ ዋጋ በማነፃፀሪነት እየተወሰደ ይሰራበት የቆየውን አፈፃፀም በተደረገው ማጣራት ከአዋጁና ከመመሪያው አንፃር የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም ይህ ደብዳቤ ወጪ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ እና ዲ/ዮናቸው በዋጋ ምክንያት በእንጥልጥል ላይ የሚገኙ ብረታብረቶች የክፍያ ሥርዓቶች በማየት በተገዛበት ቀን ወይም ደቢት ኖት ቀን (Debit Note date) እየታየ ይሰራበት የነበረውን አሠራር ቀርቶ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 እና በመመሪያ ቁጥር 111/08 በተደነገገው መሰረት በስድስቱ የዋጋ አተማመን ዘዴዎች በቅደም ተከተል በመጠቀም በሥጋት ሥራ አመራር መርህ መሠረት ተገቢውን ማጣራት በማድረግ እንዲወሰን እንዲደረግ እና የዋጋ መረጃ ማነፃፀሪያ አጠቃቀም በተመለከተ ከዚህ በፊት በቁጥር 3.1.0/544/08 በቀን 22 ታህሳስ 2008 ዓ.ም. በተጻፈ ሰርኩላር መሠረት ተገቢውን እንዲፈጸም እያሳሰብን፣ በኢ.ሲ.ቪ.ኤስ ውስጥ የሚገባው መረጃ ጥራትና ወጥነት ለማስጠበቅ ሁሉም ዲክሌራሲዮን አቅራቢዎች ወደ ቪ.ዲ.ዲ እና አሲኩዳ ውስጥ የሚያስገቡት የዕቃዎቹ ክብደት መለኪያና ብዛት መጠን በኪሌግራም ብቻ መሆኑን በማረጋገጥ እንድትሰሩ እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ፈ.ቃዱ በቀለ

ምደባ አሠራርና ፕሮግራም

ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬ...

__ግልባጭ፡__

- ለጉምሩክ ጉዳዮች ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት አ/ፐ/ልማ ዳይሬክቶሬት
- ለህግ ምክርና አስተያየት ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ጽቤት

__ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን__